የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፷፫
አዲስ አበባ ሀምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 63
ADDIS ABABA 31st July, 2015

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱፻፫/፪ሺ፯ ዓ.ም

ለአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን አውቶቡስ መስመር ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ......................ገጽ ፰ሺ፫፻፪

CONTENTS

Proclamation No. 903/2015

Agency Francaise De Development (AFD) Credit Facility Agreement for Financing the Addis Ababa City Bus Rapid Transit Project Ratification Proclamation................Page 8302

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፫/፪ሺ፯

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፀደቅ የወጣ አዋጅ

ለአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን አውቶቡስ መስመር ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፶ ሚሊዮን ዩሮ (ሃምሳ ሚሊዮን ዩሮ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል ሚያዚያ ፰ ቀን ፪ሺ፯ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፫ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION No.903/2015

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT FACILITY AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND AGENCE FRANCAISE DEVELOPMENT (AFD)

WHEREAS, the Credit Facility Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Agency Francaise Development (AFD) stipulating that Agency Francaise De Development (AFD) shall make available to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit Facility in an amount of Fifty million EURO (EURO 50,000,000) for financing the Addis Ababa City Bus Rapid Transit Project was signed in Addis Ababa , on April 16th, 2015;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Credit Facility Agreement at its session held on the 30th day of June ,2015;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለአዲስ አበባ ከተማ ፈጣን አውቶቡስ መስመር ግንባታ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፫/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ኤጀንሲ መካከል ሚያዚያ ፰ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 104601x የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፶ ሚሊዮን ዩሮ (ሃምሳ ሚሊዮን ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሀምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**
**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**



1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the "Agency Francaise De Development (AFD) Credit Facility Agreement for financing the Addis Ababa City Bus Rapid Transit Project Ratification Proclamation No. 903/2015".

2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Credit Facility Agreement signed in Addis Ababa, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Agency Francaise Development (AFD), on April 16th, 2015 AFD Agreement No.104601X is ratified.

3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit facility amount of Fifty million EURO (EURO 50,000,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Facility Agreement.

4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 31st day of July, 2015.**

**MULATU TESHOME (DR.)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**
**REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት